


# ለአነስተኛ የንግድ ሥራዎች ገንዘብ አቅርቦት

2022-2023

**New York Immigration Coalition**
nyic.org

# ማውጫ


## I. መግቢያ

የንግድ ብድር 1

## II. የንግድ ብድር

የንግድ ብድርን መረዳት 2
የንግድ ብድር መመስረት 3

## III. የገንዘብ አቅርቦት አማራጮች

ከግል ምንጭ ገንዘብ ማቅረብ 4
ጓደኞች እና ቤተሰብ 5
ከበርካታ ሰዎች ገንዘብ ማሰባሰብ (ክራውድ ፈንዲንግ) 6
ከብርካታ ሰዎች ገንዘብ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች 7
የገንዘብ እገዛ 8
ብድር 9
የብድር ማመልከቻ ማቅረቢያ ደረጃዎች 10
የአነስተኛ የንግድ ሥራዎች የብድር ማመልከቻ በጠቅላላው ቼክሊስት 11

## IV. ኃብቶች

የኒው ዮርክ ክፍለ ግዛት ማኅበረሰብ የልማት የፋይናንስ ተቋማት 12

## የዚህ መመሪያ አጠቃቀም

የአነስተኛ የንግድ ሥራዎች ምስረታ እና እድገት ቁልፍ ገጽታ የንግድ ሥራዎን ፍላጎት ለማሟላት **የሚያስችሉዎት**ን የገንዘብ አማራጮች መረዳት ነው። በውጭ አገር ዜጎች (ኢሚግራንት) ባለቤትነት ሥር ያሉ አነስተኛ የንግድ ሥራዎች በኒው ዮርክ ክፍለ ግዛት ውስጥ ካሉ የግል ሥራዎች መካከል 33.8% የሚሆነውን ይሸፍናሉ፤ ይህንን ማኅበረሰብ አግባብነት ካለው መረጃ እና የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው የአነስተኛ የንግድ ሥራዎች ባለቤቶች እና ሥራ ፈጣሪዎች ከተመደቡ ግብዓት/ምንጮች ጋር ማገናኘት የእኛ ግብ ነው።

ይህ መመሪያ የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው የአነስተኛ የንግድ ሥራዎች ባለቤቶች አጋዥ መሣሪያ በመሆን ስለ ንግድ ሥራ ክሬዲት/ብድር አመሰራረት፣ ስለ ገንዘብ አቅርቦት አማራጮች እና አጠቃላይ የብድር ማመልከቻ አቀራረብ መረጃ ይሰጣል። የሚመርጡት የገንዘብ አቅርቦት አማራጭ በንግድ ሥራዎ አወቃቀር እና የወደፊት የፋይናንስ ሁኔታዎን ይወስናል። የገንዘብ አቅርቦት የንግድ ዓላማዎን ለማሳካት እንዴት እንደሚያግዝዎ እና የፋይናንስ ፍላጎትዎን ለመሸፈን እንደሚያስችልዎ ከግምት ማስገባት ጠቃሚ ይሆናል።

ይህ መመሪያ እንደ ፈቃድ ያሉ ቅድመ ሁኔታዎችን አይሸፈንም። ይህ መመሪያ የንግድ ገንዘብ አቅርቦት ጽንሰ ሃሳብ አጠቃላይ ምልከታ ተደርጎ ጥቅም ላይ መዋል አለበት። እባክዎን ተጨማሪ ግብዓቶችን ለማግኘት የአነስተኛ የንግድ ሥራ መመሪያውን በ **https://www.nyic.org/immigrant-small-business-guide/** ይመልከቱ።

## የንግድ ብድርን ስለመረዳት

ለንግድ ሥራዎች ገንዘብ ለማግኘት ከመወሰንዎ በፊት፣ የንግድ ሥራ ክሬዲት/ ብድር መመስረት አለብዎ። **የንግድ ብድር/ክሬዲት**፣ እንደ ግል ብድር/ክሬዲት ሁሉ፣ አበዳሪዎች ለእርስዎ ብድር መስጠት ተገቢ ስለመሆኑ ለመወሰን እንዲችሉ ያግዛቸዋል። መሪዎች አንድ የንግድ ሥራ ብድር ለማግኘት ምን ያህል ብቁ እንደሆነ ወይም የንግድ ሥራው የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት ምቹ መሆኑን ለመወሰን ያስችላቸዋል። መሪዎች የንግድ ሥራዎን የፋናንስ ታሪክ እና ዕዳ ለመክፈል ያለዎትን ችሎታ በመመልከት ይህንን ማወቅ ይችላሉ።

የንግድ ብድሩ/ክሬዲት መከፈት ያለበት በንግድ ድርጅቱ ስም ነው። ይህም የንግድ ሥራዎ እና የግል ክሬዲትዎ የተለያዩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል። ይህም ከዚህ በሚከተሉት ምክንያቶች አስፈላጊ ነው፦

- የግል ብድርዎ የንግድ ድርጅትዎ ሊያጋጥመው ከሚችለው ማንኛውም አሉታዊ ተጽዕኖ እንዲጠበቅ እና ነጻ እንዲሆን ያደርገዋል።
- የንግድ ድርጅትዎ ክሬዲት/ብድር መገንባት መጀመር ይችላል፤ ይህ ደግሞ ብድሮች እና ሌሎች የገንዘብ አቅርቦት ምንጮችን የማግኘት ዕድልዎን ያሻሽላል።
- ለግብር ዓላማ እንደጠቅምዎ የንግድ ወጪዎችን በተሻለ ለመለየት ያስችልዎታል።

## የክሬዲት/የብድር ታሪክ

የክሬዲት/ የብድር ታሪክዎ በገንዘብ አቅርቦት ዕድሎች፣ በኢንሹራንስ ተመኖች ላይ ተጽዕኖ የሚያደርስ ሲሆን፣ የንግድ አጋሮች፣ አቅራቢዎች እና ነጋዴዎች ከእርስዎ የንግድ ሥራ ጋር አብረው ለመስራት ፈቃደኞች መሆናቸውን ለመወሰን እንዲችሉ ያግዛቸዋል። የክሬዲት/ብድር ታሪክ አጋሮች እና አበዳሪዎች የንግድ ሥራዎች ለማደግ እና ትርፋማ ለመሆን ይችል እንደሆነ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

እንዲሁም አበዳሪዎች የክሬዲት/የብድር ታሪክን ለንግድ ሥራ የሚሆን ብድር ማጽደቅ ያለባቸው ወይም የሌለባቸው መሆኑን ለመወሰን ያስችላቸዋል። የግል እና የንግድ ብድር ታሪኮች ለብድር ብቁ መሆንን ለመወሰን ከግምት ይገባሉ።

እንደ ኤክስፐሪን፣ ኪኩዊፋክስ፣ ዱን እና ብራንድስትሪት ያሉ የብድር/ ክሬዲት ሪፖርት አድራጊ ኤጀንሲዎች ብድርዎን/ ክሬዲትዎን ለመመርመር ከዚህ የሚከተሉትን **ጉዳዮች** ከግምት ያስገባሉ፦

| | | |
|---|---|---|
| በሥራ ላይ የቆዩባቸው ዓመታት | ላለፉት 9 ወራት ጊዜ ያመለከቱበት የብድር/ክሬዲት ላይን | ላለፉት 6 ወራት ጊዜ የተከፈቱ የብድር/ከሬዲት መስመሮች |
| የዘገዩ ክፍያዎች ብዛት | የኢንደስትሪ እና የኩባንያ መጠን | ያሉት 12 ወራት ጊዜ የክፍያ ታሪክ |

| የንግድ ክሬዲት/ብድር ስለመክፈት | |
|---|---|
| **የንግድ መዋቅር መምረጥ** | • ሁሉንም የንግድ መዋቅሮች በግል ባለቤትነት ስር ካሉት ሥራዎች ውጪ የንግድ ሥራዎን ከግል ክሬዲት የለያሉ፤<br><br>• ስለ ንግድ መዋቅሮች ከዚህ ስፍራ ማወቅ ይችላሉ፡- https://www.nyic.org/immigrant-small-business-guide/ |
| **የአሰሪ መለያ ቁጥር (EIN) ስለማግኘት** | • የአሰሪ መለያ ቁጥር (EIN) ማለት የፌዴራል የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ተብሎም የታወቃል። አንድን የንግድ ድርጅት ከሌላው ለመለየት ጥቅም ላይ ይውላል። የንግድ ሥራዎ የአሰሪ መለያ ቁጥር (EIN) ማግኘት ያስፈልገዋል። ይህም የሚያስፈልግዎ የግብር ማሳወቂያ ለማስገባት፣ የንግድ ባንክ ሒሳብ ለመክፈት እንዲሁም ለንግድ ሥራዎ ብድር እና ፈቃድ (ፐርሚት እና ላይሰንስ) ለማግኘት እንዲችሉ ነው።<br>• ለአሰሪ መለያ ቁጥር (EIN) ለማመልከት ይህንን የ IRS መገልገያ መጠቅም ይችላሉ፡-https://www.irs.gov/ein |
| **የንግድ የባንክ ሒሳብ ስለመክፈት** | የንግድ የባንክ ሒሳብ መክፈት የግል እና የንግድ ሥራዎን ወጪዎች ለመለየት ወሳኝ ነው። ከዚህም ሌላ ባንኮች ለብድር ማመልከቻዎች እንደ ማጣቀሻዎች/ምስክር ሊያገለግሉ ይችላሉ። |
| **በነጋዴዎች/አቅራቢዎች ዘንድ ክሬዲት መመስረት** | ከነጋዴዎች እና አቅራቢዎች አቅርቦቶች፣ ግብዓቶች እና ሌሎች ማቴሪያሎች መግዛት ክሬዲትዎን/ ብድርዎን ለመገንባት ያስችልዎታል። |


## ከግል ምንጭ ገንዘብ ማቅረብ

**ከግል ምንጭ ገንዘብ ማቅረብ ወይም ቡትስትራፒንግ** ለንግድ ሥራዎ ከግልዎ ምንጭ ገንዘብ ሲያቀርቡ ነው። አዳዲስ የንግድ ድርጅቶች ከራሳቸው የገንዘብ ምንጭ ለራሳቸው የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ ማቅረብ የተለመደ አይደለም፤ ስለሆነም እንደ ስቶክ፣ ኢንቬስትመንት፣ የግል ክሬዲት ካርድ ወይም ብድር የመሳሰሉ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም አለባቸው።

ከግል ምንጭ ገንዘብ መጠቀም የንግድ ባለቤቶች ውሳኔዎቻቸውን በነጻነት ለመወሰን እና ከሽያጭ እና ኢንቬስትመንት የሚያገኙትን ገቢ 100% ለመሰብሰብ እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ከግል ምንጭ ገንዘብ መጠቀሙ የንግድ ሥራው ባለቤት ሁሉንም ስጋት እና ከሥራው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ኃላፊነቶች መሸከም ይኖርበታል።

ከግል ምንጭ ያገኙትን ገንዘብ በሚጠቀሙ ጊዜ፣ የንግድ ድርጅትዎ በተቻለ ፍጥነት ትርፋማ መሆኑን ማረጋገጥ አለብዎ። ምክንያቱም ለንግድ ሥራ ያዋሉትን ገንዘብ መልሰው ማግኘት አለብዎ።

ወደ ኢንቬስተሮች ወይም ባንኮች ከመሄድ ይልቅ በራሳቸው ገንዘብ የንግድ ሥራቸውን የሚጀምሩ ነጋዴዎች ብዙውን ጊዜ ከቤተሰብ እና ጓደኞች ድጋፍ ወይም የገንዘብ አቅርቦት ይጠይቃሉ።



## ጓደኞች እና ቤተሰቦች

ጓደኞች እና ቤተሰቦች ብዙውን ጊዜ ለአነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ባለቤቶች እገዛ ያደርጋሉ፤ ይህንንም የሚያደርጉት ጓደኞች እና የቤተሰብ አባላት ከእርስዎ ጋር ግንኙነት አላቸው፣ በእርስዎ ግቦች እና ችሎታዎችም እምነት ይኖራቸዋል።

አንዳንድ የንግድ ሥራዎች ለብድር በሚያመለክቱ ጊዜ እና ኢንቬስተሮች ለማግኘት ጥረት ሲያደርጉ በሚገጥሟቸው እክሎች ምክንያት፣ ከጓደኞች እና ከቤተሰብ አባላት የገንዘብ እገዛ ማግኘት ቁልፍ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል። እነርሱም በስጦታ፣ በብድር ወይም ኢንቬስት በማድረግ የገንዘብ እገዛ ያደርጉልዎታል። ከዚህም ሌላ ከምንም ነገር ጋር ባልተገናኘ ሁኔታ ለእርስዎ ገንዘብ ሊያቀርቡ ወይም ብድር ሊሰጡዎ ይችላሉ፤ በእርሱም የሚሰጡ ብድሮች ብዙውን ጊዜ እንደ ሁኔታው የሚመቻች የብድር መክፈያ የጊዜ ሰሌዳ ያለው ነው።

ከንግድ ሥራዎ ጋር በተያያዘ ስለሚያጋጥሙዎ ስጋቶች እና ከንግድ ሥራዎ ጋር ተያያዥ ስለሆኑ ኃላፊነቶች ግልጽ መረዳት ይኑርዎ፤ ገንዘብ በሚበደሩም ጊዜ የብድሩ ሁኔታ ግልጽ እንዲሆን ያድርጉ። ከጓደኞች እና የቤተሰብ አባላት ድጋፍ በመጠየቅ ጊዜ ከዚህ የሚከተሉትን ወሳኝ እርምጃዎች ከግምት ያስገቡ፡-

| | |
|---|---|
| **ግልጽ ይሁኑ፡-** | • ለአንድ ግልጽ ግብ ግልጽ መጠን ያለው ገንዘብ ይጠይቁ። |
| **ግልጽ ይሁኑ** | • የእርስዎ ኢንቬስትመንት ምንድን ነው?<br>• የእርስዎ ግዴታዎች ምንድን ናቸው?<br>• ያሉት ስጋቶች ምንድን ናቸው? |
| **የብድሩን ይዘቶች በግልጽ በጽሑፍ ዘርዝረው ያስቀምጡ** | • የብድሩ መጠን፣ የወለድ ተመን አካትቶ<br>• የብድሩ ዓላማ<br>• የብድር መመለስ ሁኔታ - በአንድ ጊዜ ወይም በየተወሰነ ጊዜ በሚከፈል ክፍያ፤ የእያንዳንዱ ክፍያ የገንዘብ መጠን<br>• የብድር ክፍያ የጊዜ ሰሌዳ፤ በዚህም ውስጥ የብድር ክፍያው የሚጀምርበት ጊዜ እና ግልጽ የሆነ ማጠናቀቂያ ጊዜ<br>• ብድር አለመክፈል የሚያስከትላቸው ነገሮች |

## ከበርካታ ሰዎች ገንዘብ ማሰባሰብ

ከበርካታ ሰዎች ገንዘብ ማሰባሰብ ማለት ከማኅበረሰቡ ለንግድ ሥራዎ የሚሆን ገንዘብ ሲያሰባስቡ ማለት ነው። ይህም ብዙውን ጊዜ የሚደረገው በኢንተርኔት ፕላትፎርሞች አማካኝነት ነው።

ለአነስተኛ የንግድ ሥራዎ ከበርካታ ምንጮች በሁለት ዓይነት መንገድ ገንዘብ ሊያሰባስቡ ይችላሉ፡-

- በእርዳታ ላይ የተመሰረተ የገንዘብ አቅርቦት፡- ምንም የሚያገኙት ነገር ሳይኖር ለንግድ ሥራዎ የሚሆን ገንዘብ ከግለሰቦች ማሰባሰብ። ይህ አንተኛ እና ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ዘዴ ለአነስኛ የንግድ ሥራዎች እጅግ ምርጥ ዘዴ ነው።
- በምላሽ ላይ የተመሠረተ የገንዘብ አቅርቦት፡ የገንዘብ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለሚያደርጉት የገንዘብ እገዛ ማረጋገጫ ፣ ምርት ወይም አገልግሎት ያገኛሉ። ለምሳሌ፡- ለአዲሱ የዳቦ/ኬክ መጋገሪያዎ አዲስ ኦቨን ማግኘት ከፈለጉ ገንዘብ አቅራቢዎቹ ለሚያደርጉት እገዛ የአገልግሎት ዋጋ ቅናሽ ወይም ነጻ ኬክ ሊሰጡዋቸው ይችላሉ።

## ከበርካታ ሰዎች ገንዘብ የማሰባሰብ ጥቅሞች እና ጉዳቶች

ከበርካታ ሰዎች ገንዘብ ማሰባሰብ ልዩ ልዩ ጥቅሞች ይሰጣል፡- ከእነርሱም መካከል የብራንድ ግንዛቤን መጨመር፣ የደንበኛ መሠረትን ለመመስረት እገዛ ማድረግ እንዲሁም የግል የፋይናንስ ስጋትን መቀነስ ናቸው። በተመጫሪም በተመሳሰይ መልኩ ከበርካታ ሰዎች ገንዘብ ያሰባሰቡ ኩባንያዎችን በመፈለግ ስለሚያቀርቧቸው ማበረታቻዎች እነ ስኬታማ መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይችላሉ።

ሆኖም ግን ከበርካታ ምንጮች ገንዘብ ማሰባሰብ ስኬታማ የመሆኑ ወይም ያለመሆኑ ሁኔታ የሚወሰነው ሊያግዙ የሚችሉ ረዳዎችን ለማግኘት በመቻልዎ ላይ ነው።

እንደ ኪክስታርተር፣ ኢዲዬጌጎ እና ጎፍንድሚ ያሉ ፕላትፎርሞች ከበርካታ ሰዎች ገንዘብ ለማሰባሰብ ጠቃሚ ዘዴዎች ናቸው። ስለምርቱ ወይም አገልግሎቱ መረጃ መለጠፍ፣ የገንዘብ ማሰባሰቡን ግብ መወሰን እና የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ ይችላሉ። ነገር ግን አንዳንድ ፕላትፎርሞች ግቡ ካልተሟላ ገንዘቡን አይለቅቁም፤ እንዲሁም የፕላትፎርም እና የክሬዲት እና ዴቢት ካርዶች ክፍያ ይጠይቃሉ።



# ከበርካታ ሰዎች ገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕላትፎርሞች፡-

| ፕላትፎርሞች | ጥቅሞች | ጉዳቶች |
|---|---|---|
| ኪክስታርተር www.kickstarter.com | • ይህ በምላሽ ላይ የተመሠረተ ፕላትፎርም ሲሆን፣ እንደ መርቸንዳይዝ እና ቅናሽ ያሉ ማበረታቻዎችን ለደጋፊዎች ወይም ለረዷዎች ለመስጠት የሚያስችልዎ ነው።<br>• እጅግ ታዋቂ ከበርካታ ሰዎች ገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕላትፎርም | • ገንዘቡን ማግኘት የሚችሉት የማሰባሰቡ ግብ ከተሟላ ብቻ ነው<br>• የፕላትፎርም ክፍያ 5%<br>• የክፍያ ልውውጥ ክፍያ (3%-5%) |
| ጎፈንድሚ www.gofundme.com | • 0% የፕላትፎርም ክፍያ<br>• ግብዎ ቢሟላም ሆነ ባይሟላ እያንዳንዱን የገንዘብ እገዛ መውሰድ ይችላሉ<br>• 24/7 የባለሙያ እገዛ አለ | • የክሬዲትእና ዴቢት ካርድ ልውውጥ ክፍያዎች |
| ኢንዲጎጎ www.indiegogo.com | • የተወሰነ የገንዘብ ማሰባሰብ ግብ ማስቀመጥ መቻል (የሁሉም ወይም ምንም አማራጭ) ወይም ወጥነት የሌለው የገንዘብ ማሰባሰብ (ግብዎ ቢሟላም ባይሟላም ገንዘቡን ያገኛሉ)<br>• ኢንዲጎጎ ኢንዲማንድ የገንዘብ ማሰባሰቡ ዘመቻ ካበቃ በኋላም የገንዘብ ማሰባሰቡን እንዲቀጥሉበት ያስችልዎታል። | • 5% የፕላትፎርም ክፍያ<br>• የሦስተኛ ወገን የክፍያ ማካሄጃ ክፍያ |

## የገንዘብ እገዛ

የገንዘብ እገዛ የገንዘብ አቅቦት ዓይነት ሲሆን፣ ለአንድ የንግድ ድርጅት ለአንድ የተለየ ዓላማ የሚሰጥ ነው። ገንዘቡ ከመንግሥት ተቋማት ለምሳሌ ኤጀንሲዎች፣ ባንኮች/የክሬዲት ማኅበራት ወይም ለትርፍ ያልተቋቋሙ አካላት ሊገኝ ይችላል።

ብድር በሚወስዱ ጊዜ፣ አበዳሪዎች ብድሩን ለመመለስ እንደሚችሉ እና አቅም እንዳለዎ እንዲያሳዩ ይፈልጋሉ፤ ሆኖም ግን የገንዘብ እገዛ የሚሰጥዎ ኤጀንሲ የንግድ ሥራዎ ከእርሱ ተልዕኮ ወይም ከአንድ የተለየ ማበረታቻ ጋር አብሮ እንዲጣጣም ይፈልጋል። ከብድሮች በተለየ መልኩ፣ የገንዘብ እገዛዎች መልሶ መክፈልን አይጠይቁም፤ እንዲሁም የንግድ ውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ አያስከትሉም።

ሌላው የገንዘብ እገዛ ጥቅም ለአንድ የገንዘብ እገዛ ብቁ ለመሆን የክሬዲት ስታንዳርድ የማይጠይቅ መሆኑ ነው። ሆኖም ግን የገንዘብ እገዛ ብዙውን ጊዜ ጥብቅ የብቁነት መስፈርቶች ያሏቸው በመሆኑ፣ እነርሱም ማሟላት ቀላል አይሆንም፤ እንዲሁም የገንዘብ እገዛዎች በግብር ላይ የራሳቸው ውጤት ይኖራቸዋል፣ የእገዛውም አሰጣጥ መስፈርቶች ይኖሩታል። አብዛኞቹ የሚሰጡት የንግድ ሥራዎ ከገንዘብ አቅራቢው ተልዕኮ ወይም ተነሳሽነት ላይ ተመስርተው በመሆኑ፣ ለገንዘብ እገዛ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ከፍተኛ ውድድር ያለባቸው እና ስኬታማ የመሆናቸውም እድል ዝቅተኛ ነው።



## ብድሮች

ከራስዎ የገንዘብ ምንጭ ገንዘብ የማሰባሰብ አማራጭ የማይቻል በሚሆን ጊዜ፣ ብዙውን ጊዜ ቀጣዩ አማራጭ የሚሆነው ብድር ነው። የንግድ ሥራ ብድሮች የጥሬ ገንዘብ ፍሰትዎ እንዲያድግ፣ ውድ መሣሪያ እንዲገዙ እና የንግድ ድርጅትዎ እንዲያድግ ያግዝዎታል።

ከባሕላዊ የንግድ ሥራ ብድር በተለየ መልኩ፣ የአነስተኛ የንግድ ሥራ ብድሮች አነስተኛ የወለድ ተመን ያላቸው፣ ሊለዋወጥ የሚችል ቅድመ ክፍያ የሚከፈልባቸው እና ለማመልከትም ቀላል የብድር ዓይነት ናቸው።

### ብድር ለመውሰድ በመወሰን ጊዜ ከግምት መግባት ያለባቸው ጉዳዮች፡-

- የገንዘቡ አጠቃቀም
  - አበዳሪዎች ገንዘቡን በምን መልኩ እንደሚጠቀሙበት ግልጽ የሆነ ዕቅድ እንዲኖርዎ ይፈልጋሉ፤ ስለሆም ብድሩ ለምን እንዳስፈለገዎ በግልጽ ይወስኑ።

- የክፍያው መጠን
  - የሚወስዱት ብድር ወርሃዊ ክፍያውን መክፈል ይችላሉ?
  - የወለድ ብቻ ክፍያ መክፈል ይችላሉ?
  - አስፈላጊ ሆነ የብድር ክፍያውን ወደ ሌላ ጊዜ ሊያዘዋውሩ ይችላሉ?

- ወጪ
  - የወለድ ወጪዎችን መሸፍን ይችላሉ?
  - ብድሩን ከጊዜው በፊት አስቀድሞ ከመክፈል ጋር የተያያዘ ክፍያ አለን?

- የጊዜ ሰሌዳ
  - ለብድር ለማመልከት ከሁሉ የተሻለው ጊዜ ገንዘቡ ወዲያውኑ በማያስፈልግዎ ጊዜ ነው። የብድር ማመልከቻ ሂደቱ ረጅም ጊዜ ይፈጃል፤ ስለዚህም የሚያስፈልግዎትን አስቀድሞ ማወቅ ጠቃሚ ነው።



| ለብድር ማመልከቻ ደረጃዎች | |
|---|---|
| **አበዳሪዎችዎን ያነጋግሩ** | • First, start with local banks or credit unions that you have an existing banking relationship with. If a bank is not an option, city and state-sponsored loans and Community Development Financial Institutions are good alternative lenders |
| **የሚጠይቁትን የብድር መጠን ይወስኑ** | • ወጪዎችዎን ለመሸፈን ምን ያህል ገንዘብ እንደሚያስፈልግዎ ይወስኑ።<br>• ወጪዎ አንድ ጊዜ ወይም ተደጋጋሚ መሆኑን ይወስኑ። |
| **የአበዳሪውን መስፈርት ከግምት ያስገቡ** | • ማመልከቻዎን ለማቅረብ ምን ዓይነት ሰነዶች እንደሚያስልጉዎ ይወስኑ |
| **ዓላማውን ይወስኑ (ገንዘቡን የሚጠቀሙበት እንዴት ነው)** | • ለምሳሌ፡-<br>  ◦ አዲስ መሣሪያ ወይም አቅርቦቶች ለመግዛት<br>  ◦ ሕንጻ/መደብር ይግዙ ወይም ለመከራየት<br>  ◦ ለሠራተኞች ክፍያ ለመፈጸም |
| **የብድር ክፍያውን የገንዘብ መጠን ያስሉ** | • በብድሩ ከመስማማትዎ በፊት ወርሃዊ ክፍያውን መክፈል መቻልዎን እርግጠኛ ይሁኑ<br>• ብድሩን እንዴት መልሰው መክፈል እንደሚችሉ እና የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ ብድር ክፍያ ጊዜ ያስፈልግዎ እንደሆነ ይወስኑ ፤<br>• በእያንዳንዱ ወር የሚከፍሉትን የገንዘብ መጠን ለማስተካከል ይችሉ እንደሆነ ወይም ሁል ጊዜም አንድ ዓይነት መሆኑን ይወስኑ |

## የአነስተኛ የንግድ ሥራ የብድር ማመልከቻ አጠቃላይ ቼክሊስት

ለአንድ ብድር ለማመልከት ዝግጁ ከሆኑ በኋላ፣ ለብድር ማመልከቻዎ የሚያስፈልግጉዎትን የፋይናንስ እና የንግድ ሰነዶች ማዘጋጀት አለብዎ፡-

**የፋይናንስ ሰነዶች**
ከዚህ የሚከተሉትን የቅርብ ጊዜ ማስረጃዎች ማቅረብ አለብዎ

- የግል እና የንግድ ግብር ክፍያ ሰነዶች
- የፋይናንስ መግለጫ፣ ከእነርሱም መካከል
  - የትርፍ እና ኪሣራ መግለጫ፣ የሐብት ሚዛን ማሳያ እና የገንዘብ ፍሰት መግለጫ
- የግል መግለጫዎች፣ ከእነርሱም መካከል
  - የማኅበራዊ ዋስትና ቁጥር ወይም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የክሬዲት/ የብድር ታሪክ፣ የልውውጥ ታሪክ እና የክፍያ እና የተንቀሳቃሽ ሒሳብ መረጃ

**የንግድ ሰነዶች**

- የንግድ መዋቅር እና የሕግ ሰነዶች
  - መመስረቻ ጽሑፍ
  - የንግድ ምዝገና እና የንግድ ፈቃድ
  - መተዳደሪያ ደንብ እና አሰራር መመሪያ
  - ተከራይተው የሚሰሩ ከሆነ፣ የተከራዩት ቦታ ወይም የመሣሪያው ኪራይ ማስረጃ ቅጂ
- የቢዝነስ ዕቅድ
  - ይህ የንግድ ሥራዎ ኢንቬስት ሊደረግበት እንደሚገባ ለአበዳሪዎች የሚገልጹበት ዕድል ነው። ይህም የፋይናንስ ትንበያ፣ የተልዕኮ መግለጫ እና ስትራቴጂ ያካትታል።

**ለብድር ማመልከቻዎች አስፈላጊ ስለሆኑ የፋይናንስ እና የንግድ ሰነዶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን ይጎብኙ፡-**
**https://www.sba.gov/funding-programs/loans/7a-loans**

## NYS የማኅበረሰብ ልማት የፋይናንስ ተቋማት (CDFIs)

የማኅበረሰብ ልማት የፋይናንስ ተቋማት በውጭ አገር ዜጎች፣ በሴቶች ባለቤትነት ስር ላሉ የንግድ ሥራዎች እና አነስተኛ ገቢ ላላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ዝቅተኛ ወለድ ያላቸው ብድሮች፣ የገንዘብ እገዛ ዕድሎች እና እንደ አንድ ጊዜ የምሪት እና ሥልጠና ፕሮግራም ያሉ ፕሮግራሞች አማካኝነት እገዛ ይሰጣሉ።

የማኅበረሰብ ልማት የፋይናንስ ተቋማት (CDFIs) የገንዘብ አቅርቦትን ለመፈተሽ ጥሩ ምንጮች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን አነስተኛ የንግድ ሥራ ስለመጀመር፣ የገንዘብ አቅርቦት ስለመድረግ እና ስለማሳደግ ጥሩ የመረጃ ምንጭ ነው። ከዚህ በማስከተል በኒው ዮርክ ክፍለ ግዛት ያሉ ፣ በእርስዎን በንግድ ሥራዎ ሊያግዙዎ የሚችሉ የማኅበረሰብ ልማት የፋይናንስ ተቋማት ይገኛሉ፦

| | |
|---|---|
| **አካምፓኒ ካፒታል**<br>Accompanycapital.org | **ቢኦሲ ካፒታል**<br>Boccapital.org |
| **ሬናይሳንስ ኢኮኖሚክ ዲቨሎፕመንት ኮርፖሬሽን**<br>renaissance-ny.org | **ፐርሱት**<br>https://pursuitlending.com/ |
| **TruFund Financial Services**<br>https://www.trufund.org/ | **በኒው ዮርክ ውስጥ የሚገኙ ተጨማሪ የማኅበረሰብ ልማት የፋይናንስ ተቋማት ን ከዚህ የሚከተለውን ድረ ገጽ በመጎብኘት ሊያገኙ ይችላሉ፦**<br>https://www.nyscdfi.org/nyscdfis |